# የአዲስ አበባ መንገድ ልክ እንደ ገጠሩ የአፍርና ውሀ እቀባ ስራ በየጊዜው ከመቆፈር ዘላቂ ፤ዘላቂ፤ዘላቂ፤ መፍትሄ ቢሰጠውስ!!!!!

ይድረስ ለሚመለከተው !!!!!!!!!

እጅግ በጣም የሚገርመኝ እና የሚያሳዝነኝ ነገር በአዲስ አበባ በርካታ መንገዶች ይሰራሉ ፤ይጠገናሉ ወዘተ፡፡ ግን ደግሞ በሀላፊነት በተቀመጡ ሰዎች እውቀት ማነስ ይሁን፤ ቁርጠኝነት ማነስ እንዲሁም የህብረተሰቡ ቸልተኝነት መንገዶቹ ዝናብ በመጣ ቁጥር ውሀ ይሞላቸዋል፡፡ ምክንያቱንም ከግራ እና ከቀኝ በኩል ያሉት ጠባብ መንገዶች የሚዘንበው ዝናብ ከነአፈራቸው እና ቆሻሻቸው ወደ መንገዱ ይዘው ይገባሉ ምክንያቱም የጎን የውሀ መፋሰሻ (drainage) የላቸውም ይህ ደግሞ በየአመቱ የሚታይ ትእይንት ነው፡፡

በጣም የሚያሳስበኝ ልክ አንዳንድ አገሮች የምንሰማው ከፍተኛ ዝናብ ቢዘንብ አዲስ አበባ ሳስብ ይዘገንንኛል በመስቀል አደባባይ፤ በፍል ውሀ፤ በልደታ፤ በቁራ፤ በበቅሎቤት በላነቻ ትንሽ ዝናብ ጠብ ሲል የሚፈጠረው ጎረፍ ላስተወለ በጣም አሳሳቢ ነውና የሚመለከተው አካል አንድ ይበል፡፡ አስቲ ግንቦት ግንቦት 5/2009 ዓ.ም ዛሬ ዘጠኝ ሰአት አከባቢ ትንሽዝናብ ዘንቦ በላንቻ የባቡር መሻገሪያ ያነሳሁትን ፎቶ እንኳን ሰው መኪኖቸም ተቸግረው ሳይ እስቲ ሰሚ ካለ ላካፍል ብየ የነሳሁትን እንሆ ላካፍላችሁ እና አከባቢውን ለማያቁ መሪዎቻችን አዳርሱት፡፡

ይህ እንግዲህ ዋናው የክረምት ዝናብ ሳይጀምር ነው ክረምቱ ሲጀምር ደግሞ ውሀው በባቡር መንገዱ ዘሎ ሲሄድ እናየው ይሆናል ፡፡





